## *ለፀርብ የጸሎት አገልግሎት - ሰላም ለእናንተ ይሁን!*

በቅርቡ አንድ ትልቅ የእግዚአብሔር አገልጋይ የሚከተለውን ጥያቄ ለጸሎት ሰዎች አቀረቡ። ሁሌ ለመጸለይ በምትንበረከኩበት ጊዜ ትልቅ ተአምራዊ (Super-natural) የሆነ ነገር ይሆናል ብላችሁ ትጠብቃላችሁ? ወደ ጸሎት ቦታ የምትገቡት ከእግዚአብሔር ተአምራት ይሆናል ብቻ ሳይሆን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ውስጥ ሆኖ ተአምራትን ያመጣል ብላችሁ ትጠብቃላችሁ? ይህን የማትጠብቁ ከሆነ ከዛሬ ጀምሮ አሁን ከምታነቡት ምስክርነት እና ትምህርት የተነሳ በሕይወታችሁ ትልቅ የመንፈስ ቅዱስን መጠማት እና የመንፈስ ቅዱስም በእናንተ ውስጥ ሆኖ ታላቅ የሆነውን የእግዚአብሔርን ዓላማ መሥራት ትለማመዳላችሁ። ከዚህም በኋላ ያለዚህ ዓይነት ጥማት እንደማትጸልዩ እርግጠኛ ነኝ።

ለምንድ ነው ይህ መነቃቃት አስፈላጊ የሆነው? ዛሬ የምንኖርበት ዓለም በጣም የሚያስፈራ ነው። ያለንበት ጊዜ ለምን መጸለይ እና እንዴት መጸለይ እንዳለብን አናውቅም። ለቤተሰቦቻችን፣ ለቤተክርስቲያን እና ለዓለም ሕዝቦች እንዴት መጸለይ እንዳለብን አናውቅም። የእግዚአብሔርን ፈቃድ መጸለይ ካለብን (ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን) ከኛ ከሚገባን ከፍ ባለ መንገድ መጸለይ አለብን። የእግዚአብሔርን ተአምራት ሊያመጣ በሚችል መንገድ መጸለይ አለብን።

ይህን ማድረግ እንዴት ነው የምንችለው? ለዚህም መንገዱ አንድ ነው፣ ያም ለመንፈስ ቅዱስ ቅድሚያ መስጠት ነው። ሁሌ ለጸሎት ስንመጣ መንፈስ ቅዱስን ቅድሚያ በመስጠት በእሱ ምሪት መፀለይ አለብን። ይህም ማለት በልሳን መጸለይን መለማመድና መጀመር አለብን። ጌታ ወደ መስቀሉ ከመሄዱ በፊት በሱ ለሚያምኑት በዮሐንስ ወንጌል (ዮሐ 14፥16-18፣26) ይህን ተናገረ፦ እኔም አብን እለምናለሁ፣ ለዘላለም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል፣ እርሱም ዓለም የማያየውና የማያውቀው ስለሆነ ሊቀበለው የማይቻለው የእውነት መንፈስ ነው። ነገር ግን ከእናንተ ዘንድ ስለሚኖር፣ በውስጣችሁም ስለሚሆን እናንተ ታውቃላችሁ። .... አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል፣

እኛ ዛሬ ለተአምራት (Super-Natural) ነገር በር መክፈት አለብን። ጌታ እርሱ ቃል ኪዳን ገብቶልናል። መንፈስ ቅዱስም በእኛ ውስጥ ይኖራል። ደግሞም ሲመራን ሁሉን እናውቅ ዘንድ ምልክት ይሰጠናል። መንፈስ ቅዱስ ሁሉን ነገር ያስተምራችኋል፣ ብሎ ቃል ገብቶልናል፤ እነዚህ ቃል ኪዳኖች እንዲፈጸሙ ጌታ በተናገረው ላይ እምነት እንዲኖረን ያስፈልጋል። መንፈስ ቅዱስ ጌታ እንዳለን እንደሚያደርግ እና ይህንን ታላቅ የእግዚአብሔር ሥራ ኃይል እንደሚሰራ በደንብ ማመን አለብን። ብዙ ጊዜ በራሳችን አእምሮ ስለምንጸልይ ይህንን ማድረግ እንዘነጋለን። የጸሎት ጊዜአችንን በራሳችን ሀሳብና ቃሎች ሞልተን ለመንፈስ ቅዱስ ቦታ ሳንሰጠው እንቀራለን። ከዚህም የተነሳ መንፈስ ቅዱስ በኛ ውስጥ ሆኖ ሊሰራ የሆነው የእግዚአብሔር ዓላማ ሳይሆን ይቀራል።

***የሱነማዪቱ ሴት ምሳሌነት፡*** ከአሁን ጀምሮ በፀሎት ሕይወቴ ለመንፈስ ቅዱስ ቅድሚ ልሰጥ ወስኛለሁ። ሁላችን ልክ እንደ ሱነማዪቱ ሴት ለመሆን መወሰን አለብን (2ኛ ነገ. 4፥9) ሱነማዪቱ ሴት ለእግዚአብሔር መንፈስ በሕይወቷ ትልቅ ቦታ ልትሰጠው ወስና ስለ ነበር ነብዩ ኤልሳዕ በቤቷ በኩል ሁሌ ባለፈ ቁጥር ምግብ እንዲበላ አጥብቃ በለመነችው መሰረት ወደ ቤቷ ምግብ ለመብላት ይገባ ነበር። የኤልሳዕን በቤቷ መገኘት በጣም ትፈልገው ነበር (በይበልጥም ደግሞ በሱ ውስጥ ሆኖ የሚሰራውን የእግዚአብሔር መንፈስ)። ከዚያም በኋላ ባለቤቷን እንዲህ ብላ ተናገረችው (2ኛ ነገ. 4፥9-10) "ይህ በእኛ ዘንድ ሁልጊዜ የሚያልፈው ቅዱስ የእግዚአብሔር ሰው እንደሆነ አውቃለሁ። ትንሽ ቤት በሰገነቱ ላይ እንስራ፣ በዚያም አልጋ፣ ጠረጴዛ፣ ወንበርና መቅረዝ እናኑርለት፣ ወደ እኛም ሲመጣ ወደዚያ ይገባል" አለችው። ወንበር የሚለው ቃል በዕብራውያን ሲተርጎም ዙፋን ማለት ነው። ስለዚህ ይህቺ ሴት መንፈስ ቅዱስን በቤቷ አነገሰችው ማለት ነው። በሕይወቷ ለእግዚአብሔር ትልቅ ቦታ ሰጠችው።

ይህ ደግሞ የብሉይ ኪዳን ሀሳብ ብቻ አይደለም። ጌታ እራሱ በሉቃስ ወንጌል (ሉቃ. 14፥7-11) ወደ ሰርግ ስትጋበዝ ከፊት ከሆነ ከፍ ካለ ቦታ አትቀመጥ አለ። እንዲያውም እኛ ዝቅ ያለ ቦታ እንድንቀመጥ፣ በዚያ ለታላቅ ለሆነው እንግዳ የከበረውን የፊት ቦታ እንድንለቅ አስተምሮናል። ይህንን ስርዓት በጸሎት ሕይወታችን ላይ ማድረግ ስንጀምር መንፈስ ቅዱስ በጸሎት ቦታም ላይ የከበረ እንግዳ መሆን እንዳለበት እንገነዘባለን። ስለዚህ በዚህ በዐርብ የጸሎት ጊዜ የከበረው እንግዳችን መንፈስ ቅዱስ መሆን ይገባዋል። ሱነማዊቱ ሴት ያደረገችው ይህንኑ ነበር። መንፈስ ቅዱስን በሕይወቷ ከፍ አደረገችው፣ አነገሰችው። ከዚያም የተነሳ ታላቅ የሆነ ተአምራት በህይወቷ መለማመድና መምጣት ጀመረ። ተአምራት ፍለጋ አልሄደችም፣ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን ከፍ አድርጋ ማክበር ስትጀምር ተአምራት እየፈለጋት በሕይወቷ መምጣት ጀመረ። ኤልሳዕ ምን በማድረግ ሊባርካት እንደሚችል መጠየቅ ጀመረ። ለንጉሱ ወይም ለጦር ሰራዊት አለቃ ልንገርልሽ? አላት። እርሷ ግን ምንም ነገር አልፈለገችም ነበር። ሆኖም ኤልሳዕ ግን ሊባርካት ወስኖ ነበር (2ኛ ነገ. 4፥14-17) ኤልሳዕም እንግዲህ ምን እናድርግላት? አለ። ግያዝም፦ ልጅ የላትም፣ ባልዋም ሸምግሏል ብሎ መለሰ። እርሱም፦ ጥራት አለ። በጠራት ጊዜ በደጃፉ ቆመች። እርሱም፦ በሚመጣው ዓመት በዚህ ወራት ወንድ ልጅ ትታቀፊያለሽ አለ። እርስዋም፦ አይደለም ጌታዬ፥ የእግዚአብሔር ሰው ሆይ፥ ባሪያህን እንዳትዋሻት እለምንሃለሁ አለችው። ሴቲቱም ፀነሰች፥ በዚያም ወራት በአዲሱ ዓመት ኤልሳዕ እንዳላት ወንድ ልጅ ወለደች። ሱነማዊቱ ሴት ልጅ ልውለድ ብላ አልጠየቀችም። ትፈልግ ነበር፣ ነገር ግን ልጅ ይስጠኝ ብላ ከሱ መጠየቅ ወይ ማሰብ በጣም የራቀ ነገር ነበር። መንፈስ ቅዱስ ነበር ግያዝን በመጠቀም ይህን ሀሳብ ያመጣው። መንፈስ ቅዱስ ሃሳቡን አመጣ፣ መልሱንም ፈቀደ። ይህም ተአምር ነው። የእግዚአብሔር እጅ ነው የተንቀሳቀሰው። ነገር ግን ታሪኩ በዚህ አላለቀም። ከትንሽ ጊዜ በኋላ ልጇ ታሞ በእጇ ላይ እንደሞተ እናውቃለን። በጣም የሚያሳዝን ነገር ነው የሆነው። ሱነማዊቱ ሴት ለእግዚአብሔር መንፈስያላት ክብር እና ቅድሚያ መስጠት አልተለወጠም ነበር። ባሏን ሳታማክር(ሳታናግር) አህያዋን አስጭና ወደ እግዚአብሔር ሰው ወደ ቀርሜሎስ ተራራ ወጣች (2ኛ ነገ. 4፥26) ይህች ሱነማይት ሴት ኃይለኛ የሆነ ጭንቀት ላይ እንደነበረች ግልጽ ነው። ሆኖም ግን ተአምራትን መሥራት በሚችለው እግዚአብሔር ላይ ተስፋ አልቆረጠችበትም ነበር። በጣም ጨለማ በሆነበት ጊዜ ከእግዚአብሔር መልስ እንደሚኖር ስለአመነች ተስፋዋን አልጣለችም። ተስፋ በሌለበት ቦታ ላይ ተስፋ ይዛ ለእግዚአብሔር አሁንም ቅድሚያ ሰጠች። እግዚአብሔርም አላሳፈራትም፣ ኤልሳዕ ወደ ቤቷ ሄዶ ልጁ ላይ በመተኛት መንፈስቅዱስም ልጁን ከሞት አስነሳው።

ዛሬ እኛ የዚህ ዘመን አማኞች የዚህ ዓይነት የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ በሕይወታችን እንዲሰራ ያስፈልገናል። ይህ የትንሣኤ ኃይል (Resurrection Power)በሕይወታችን እንዲመጣና እንዲሰራ በጸሎታችን እንዲገለጽ ያስፈልጋል። መንፈስ ቅዱስ ስንጸልይ በኛ ውስጥ ሆኖ ተአምራት እንዲደረግና የሞቱ ከተሞችና አገሮች በእግዚአብሔር ኃይል ክብር እንዲነሱ እንዲደረግ መጸለይ አለብን። እኛ ከምናስበው በላይ መጸለይ ለሚችለው መንፈስ ቅዱስ ቅድሚያን በጸሎት ቦታ ላይ መስጠት አለብን። ይህንን ማድረግ ለሱ ይቻለዋል፣ ነገር ግን ይህን አምነን ሁሌ ክቡር ለሆነው ለእግዚአብሔር መንፈስ ቅድሚያ እንስጠው።

ዛሬ አምናለሁ፣ አሁን ያለንበት ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ "የመጨረሻ ጊዜ" ብሎ የሚጠራው ጊዜ ነው። የእግዚአብሔር ሙሉ ፍላጎት ነፍሳትን ወደ ልጁ መንግስት ማምጣት ነው። በእግዚአብሔር መንግስት ውስጥ ሁለት ዓይነት ወራቶች አሉ፦ የጌታ መምጣትና ለመምጣቱ መሰናዳት የሚደረግበት ጊዜያት ማለት ነው። በነዚህ ወራቶች መንፈሳዊ መንገድ የሚሰራበት ጊዜ ነው። መንገዱም የእግዚአብሔር ዓላማ በሰዎች ልብ፣ በአገሮችና በሕዝብ ላይ እንዲያልፍ የሚዘጋጅ ጎዳና ነው። እኛ አማኞች የጸሎት ጥሪ የተቀበልን የመንገዱ (የጎዳናው) ገንቢና ሰራተኞች ነን። እኛ ጸሎት አገልጋዮች የጌታን መመለስ መንገድ እንድናዘጋጅ እግዚአብሔር ጠርቶናል። መጀመሪያ የጌታን መምጣት ለማሰናዳት ዮሐንስ መጥምቁ እንደተጠራና እንደተቀባ እኛ እንዲሁ ተቀብተናል። ዮሐንስ መጥምቁ የመንፈሳዊ ጎዳና ለጌታ ያሰናዳ ሰው ነበር።ጌታ ብዙዎችን መድረስ እንዲችል መንገዱን ያዘጋጀ ታላቅ የእግዚአብሔር ሰው ነበር።

የሰራው መንገድ በጣም ትልቅ ጎዳና ነበር። ከዚህም የተነሳ ብዙዎች ከጌታ ትምህርት ተካፋይ ሊሆኑ በቅተዋል።

እንዴት ይሆን ይህንን ታላቅ መንገድ የሰራው? የሰራው ልክ ዘካርያስ 4፥6 ላይ እንደሚለው በኃይል አይደለም፡ በብርታትም አልነበረም። ነገር ግን በእግዚአብሔር መንፈስ ኃይል ነበር። ይህን ያደረገው በመስበክ ብቻ አልነበረም። ግን በላዩ ላይ ያለውን ቅባት በመጠቀም ነበር። በሱ ላይ የነበረው ቅባት ብርሃንን ከጨለማ መለየት ይችል ነበር። ሰዎችን ወደ ንሰሃ ማምጣት ይችል ነበር። ወደ እግዚአብሔር መንግስት ለመግባት ማሰናዳት ይችል ነበር። በዚህ ቅባት ያገለገለው የመጀመሪያው አገልጋይ የብሉይ ኪዳን ነብይ ኤልያስ ነበረ (ሉቃስ 1፥17) ዮሐንስም በኤልያስ መንፈስና ኃይል እንዳገለገለ ይናገረናል። በያዕቆብ 5፥16-18 እኛን መጸለይ የምንችል ጌታን አዳኝ አድገን የተቀበልን ሁሉ ከኤልያስ ጋር አመሳስሎ ጽፎልናል። ... የፃድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደጋለች። ኤልያስም እንደ እኛ ሰው ነበር፤ ዝናብም እንዳይዘንብ አጥብቆ ጸለየ፥ በምድርም ላይ ሦስት ዓመት ከስድስት ወር አልዘነበም፤ ሁለተኛም ጸለየ፥ ሰማዩም ዝናብን ሰጠ፤ ምድሪቱም ፍሬዋን አበቀለች።

የጸሎት አገልግሎት ለቤተክርስቲያናችን በጣም አስፈላጊ ቁልፍ ነው። ከዚህ የጸሎት አገልግሎት ትልቅ የመንፈሳዊ ዕንቅስቃሴ (Revival) እንደሚነሳ በጣም የተሞላ ዕምነት አለን። ለመንፈስ ቅዱስ በጸሎታችን ቅድሚያ ከሰጠን እግዚአብሔር የተከፈተ ሰማይ ሰጥቶናል። ዛሬ የእግዚአብሔር ቃል መገለጽና የእግዚአብሔር መገኘት በቤተክርስቲያን ውስጥ ጀምሯል፤፤ ለዐይን ታይቶ የማይታወቅ የመንፈስ ቅዱስ መገለጥ የሚታይበት ጊዜ ነው። እኛም ዛሬ እግዚአብሔርን በሙሉ ልብ ተጠምተን የሱን መገኘት የምንፈልግበት ጊዜ ነው። ክርስቶስን መምሰል የሁላችንም ትልቅ ጥሪ ነው። ይህ የሁላችንም ትልቅ ጥሪ መሆን አለበት። በዓለም ያሉ ያልዳኑት ጌታን ለማየት የሚችሉት በእኛ ውስጥ ያለውን ጌታ ነው። ሌላ ዕድል የላቸውም።

በጸሎታችን የምንጸልይላቸው የዓለም መሪዎች ወይም ሕዝቦች ሰላም እንዲመጣ ብቻ ሳይሆን ሁልጊዜም ማወቅ ያለብን የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል እንዲሰራጭ ነው። ለእግዚአብሔር መንግስት መንገድ (ጎዳና) እያነጽን ነው። እግዚአብሔር እኛ በምንሰራው መንፈሳዊ ጎዳና ተጠቅሞ ወንጌል ለዓለም እንዲደርስና ብዙዎች ከዘላለማዊ ሞት እንዲተርፉ ይሆን ዘንድ ነው። በዚህ ነገር ላይ ጊዜ ማጥፋት አንችልም። ቀድም ብሎ እንደተገለጸው ሁለት ዓይነት ወራት ናቸው ያሉት፥- አንዱ ወራት ለወንጌል መሰራጨት መንገድ የምንሰራበት ሲሆን፤ ሌላው ወራት ደግሞ እየመጣ ያለው የጌታ ወራት ማንም የማይሰራበት ጊዜ ነው (ዮሐንስ 9፥4) እባካችሁ መሥራት በሚቻልበት ወራት ላይ እንስራበት! እንጸልይ፥ ብዙዎች በቢሊዮን የሚቆጠሩ ጌታን የማያውቁ ነፍሳት እንዲድኑ ለእግዚአብሔር በጣም ትልቅ ጎዳና እንስራለት።

| |
|---|
| ጸሎት ላይ በመሳተፍ የምታገለግሉ ሁሉ እባካችሁ የ e-mail አድራሻ ወይም የስልክ ቁጥራችሁን ብትሰጡን፤ በዚህ ባለንበት የመጨረሻው ጊዜ በጣም ትልቅ ሥራ ይጠብቀናል። አብረን ብዙዎችን ተናጥቀን ከእሳት እናውጣ። |

# የዐርብ የፀሎት አገልግሎት

## ማርች/ኤፕሪል 2006